
የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር

የ2019 በጀት ዓመት የዜጎች በጀት መረጃ ሰነድ



ሐምሌ 2018 ዓ.ም

አዲስ አበባ

ይዘት

ምስጋና 3

1. መግቢያ 3

1.1. የዜጎች በጀት መረጃ ሰነድ ምንነት ? 4

1.2. መንግስት የዜጎች በጀት መረጃ ሰነድን ለምን ያዘጋጃል? 4

2. ስለመንግስት በጀትና የበጀት አሰራር (አስተዳደር) ስርዓት 4

2.1. የመንግስት በጀት ምንነትና አስፈላጊነት 4

2.1.1. የመንግስት በጀት ስንል ምን ማለታችን ነው? 4

2.1.2. የመንግስት በጀት ለሁለንተናዊ ልማት የሚጫወተው ቁልፍ ሚና 4

2.1.3. የመንግስት በጀት ለምን ይዘጋጃል? 5

2.1.4. የመንግስት በጀት ዝግጅትና አፈጻጸም ሂደት 5

2.2. የመካከለኛ ዘመን የወጪ ማዕቀፍ ዝግጅት (የፋይናንስ ዕቅድ ዑደት) 5

2.2.1. የበጀት ዑደት 6

2.2.2. የፋይናንስ የጊዜ ሠሌዳ 7

3. ዜጎች በበጀት ዝግጅት ሂደት እንዴት ይሳተፋሉ? 8

4. የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የ2019 በጀት ዓመት በጀት 11

4.1. የከተማ አስተዳደሩ በጀት እንዴት ነው የሚዘጋጀው? 11

4.2. ከ2018-2020 በጀት ዓመት የገቢ ትንበያ 12

4.3. ከ2019-2021 በጀት ዓመት የወጪ ትንበያ 13

የከተማው ገቢ 13

4.4. የከተማው አስተዳደር ለ2019 በጀት ዓመት የጸደቀ በጀት 13

4.5. የከተማ አስተዳደሩ የበጀት ምንጮች 14

4.6.1. የበጀት ድልድል ስርዓት 14

4.6.2. ለማዕከል ባለበጀት ተቋማት የተመደበ በጀት 15

4.6.3. የክ/ከተሞችና ወረዳዎች በጀት ድጋፍ (ድጎማ) 15

4.6.4. በወጪ ዕቅድ ትኩረት የተሰጣቸው ሴክተሮች/ዘርፎች 16

4.6.5. ልዩ ትኩረት የተሰጣቸውና ከፍተኛ በጀት የተመደበላቸው ድህነት ተኮር ፕሮግራሞች 17

4.7. ገቢን ከማሳደግና ወጪን ከመቆጠብ አኳያ የተወሰዱ አዳዲስ የፖሊሲ እርምጃዎች 19

ማጣቀሻ/ዋቢ 22

ለበለጠ መረጃ፡ 23

የቢሮ ኃላፊ መልዕክት



አቶ አብዱልቃድር ሬድዋን
በምክትል ከንቲባ ማዕረግ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳዳር ፋይናንስ ቢሮ ኃላፊ

የተከበራችሁ የከተማችን ነዋሪዎች፣ የልማት አጋሮችና ባለድርሻ አካላት!

በቅድሚያ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፋይናንስ ቢሮ ስም ላለፉት ዓመታት ለአጠቃላይ የከተማችን ልማትና መልካም አስተዳደር መረጋገጥ ላደረጋችሁት ያልተቆጠበ አስተዋጽኦና ድጋፍ የላቀ ምስጋናዬን ማቅረብ እወዳለሁ።

ተቋማችን የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፋይናንስ ቢሮ በህግ በተሰጠው ስልጣንና ተልዕኮ መሰረት፣ የከተማችንን ሀብት በብቃት፣ በግልጽነትና ባለቤትነት ስሜት የማስተዳደር እንዲሁም የህዝባችንን ሁለገብ የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ልማት ጥያቄዎች የሚመልሱ የበጀት ስትራቴጂዎችን የመቀየስ ኃላፊነት አለበት።

የኢፌዴሪ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 12 እንደሚያስረዳው የሕዝብ ተወካዮችና የሕዝብ አገልጋዮች አሠራር ለሕዝብ ግልጽ መሆን እንዳለበትና ማናቸውም የመንግሥት ኃላፊነት ያለበት አካል ለሕዝብ ተጠያቂነት እንዳለበት ተደንግጓል። በተጨማሪም በተሻሻለው የከተማችን ማቋቋሚያ ቻርተር አዋጅ ቁጥር 361/1995 ፣ በከተማ አስተዳደሩ ፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 51/2009 እና እንዲሁም በፋይናንስ ግልጸኝነትና ተጠያቂነት መመሪያ ቁጥር 05/2011 የተጣሉብንን ግዴታዎች መሰረት በማድረግ፣ የመንግስት ፋይናንስ አሰራር ግልጽነት ያለው፣ ህዝባዊ ተሳትፎን የሚያረጋግጥና ተጠያቂነትን የሚያሰፍን እንዲሆን እየሰራን እንገኛለን። የዜጎች በጀት ሰነድ ማዘጋጀትም የዚሁ ህገ-መንግስታዊና ህጋዊ ግዴታችን አካል ነው።

የተከበራችሁ የከተማችን ነዋሪዎች! ይህ የዜጎች በጀት ሰነድ የከተማችን አስተዳደር ሀብት እንዴት እንደሚሰበሰብና ለዜጎች ፋይዳ ላላቸው ተግባራት እንዴት እንደሚወል የሚያሳይ የታማኝነትና የግልጽነት መድረካችን ነው። ይህን ሰነድ በማንበብ፣ በመገምገምና አስተያየት በመስጠት የከተማችንን ሁለገብ እድገት በጋራ እንድናፋጥን ጥሪዬን አቀርባለሁ።

ለተሻለች፣ ለበለጸገችና ለነዋሪዎቿ ምቹ ለሆነች አዲስ አበባ በጋራ እንሰራለን!

ምስጋና

ይህ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የ2019 በጀት ዓመት የዜጎች በጀት መረጃ ሰነድ በወቅቱ እንዲዘጋጅ የፋይናንስ ቢሮ አመራሮች ላደረጉት ትኩረትና ድጋፍ ልባዊ አክብሮታችንን እንገልጻለን።

ለሰነዱ ዝግጅት ወቅታዊና አስፈላጊ መረጃዎችን በመሰብሰብ፣ በማደራጀትና በመተንተን ከፍተኛ አስተዋጽኦ ላበረከቱት የፊስካል ፖሊሲ እና ገቢ ጥናት ዳይሬክቶሬት ባለሙያዎች፣የቻናል አንድ ፕሮግራም ማስተባበሪያ የከተማ ልማታዊ ሴፍቲ ኔት ፕሮጀክት ባለሙያዎች፣የፋይናንስ ግልጽነትና ተጠያቂነት እንዲሁም የማህበራዊ ተጠያቂነት ባለሙያዎች የላቀ ምስጋናችንን እናቀርባለን።

በተጨማሪም በተዘጋጀው የዜጎች በጀት ረቂቅ ሰነድ ላይ ገንቢ ሃሳቦችንና አስተያየቶችን ለሰጡን ባለድርሻ አካላት ሁሉ የከበረ ምስጋናችንን እናቀርባለን።

1. መግቢያ

የከተማ አስተዳደሩ የበጀት ስርዓት መንግስት በፋይናንስ የጊዜ ሰሌዳ መሰረት በእያንዳንዱ የበጀት ዓመት የሚከናወኑ ተግባራትንና የማስፈጸሚያ ሀብትን አመጣጥኖ የሚያቅድበት ነዉ፡፡ በዚህም የመንግስት በጀት የሚያመለክተው መንግስት በበጀት ዓመቱ የሚሰበስበዉን ግብርና ሌሎች ገቢዎች፣ ለዜጎች የሚቀርቡ አገልግሎቶችን ማሟላት የሚያስችል የኢኮኖሚ ዕድገቱን ማፍጠንን፣ ተጨማሪ የስራ ዕድሎችን የሚፈጥርበት፣ የመሰረተ ልማቱን የሚያስፋፋበትና ድህነትንና ኢፍትሓዊነትን የሚያጠፋበት ሂደት ሲሆን፤ እነዚህን ውሳኔዎች ተፈጻሚ ለማድረግ በበጀት ዓመቱ ጥቅም ላይ እንዲዉል የተፈቀደዉን በጀት ለሁሉም ሊገባ በሚችል መልኩ የዜጎች በጀት መረጃ ሰነድን በማዘጋጀናት ተደራሽ በማድረግ የዜጎችን ሁለንተናዊ ተሳትፎ እንዲረጋገጥ ማድረግ ነው፡፡

1.1. የዜጎች በጀት መረጃ ሰነድ ምንነት ?

የዜጎች በጀት ሰነድ ማለት ነዋሪው ህብረተሰብ መንግስት ከተለያዩ የገቢ ምንጮች በዋናነት ከታክስ እና ታክስ ካልሆኑ ገቢዎች ሰብስቦ የህብረተሰቡን የልማትና የአስተዳዳር ወጪዎች ለመሸፈን የሚያወጣው ወጪ አመዳደብ እና አጠቃቀምን ለህብረተሰቡ ቀለል ባለ አቀራረብ የሚሳይ ሰነድ ነው።

ይህ በፋይናንስ ቢሮ ተዘጋጅቶ ለዜጎች የሚቀርበው የዜጎች በጀት መረጃ ሰነድ የመንግስት በጀት ሂደት ማለትም የበጀት ዝግጅትን፣ በጀትን ማጽደቅ፣ በጀትን ስራ ላይ ማዋልንና ስራ ላይ የዋለን በጀት እንዴት ቁጥጥር እንደሚደረግና በእያንዳንዱ ሂደት ኃላፊነት የተሰጠው አካልና የስራ ድርሻ ምን እንደሆነና ዜጎችም በዚህ የበጀት ሂደት እንዴትና መቼ መሳተፍ እንዳለባቸው በጥቅል በማመልከት በ2019 በጀት ዓመት የዜጎችን ቅድመ-ፍላጎቶች እና የከተማው አስተዳደሩ የትኩረት አቅጣጫ መሰረት የተመደባውን በጀትና በበጀቱ የሚከናወኑ አንኳር ጉዳዮችን ለከተማ ነዋሪዎች/ዜጎች የሚያስረዳ ነው፡፡

1.2. መንግስት የዜጎች በጀት መረጃ ሰነድን ለምን ያዘጋጃል?

ዜጎች ስለ መንግስት በጀት ምንነትና አሰራር በቂ ግንዛቤ ኖሯቸው መንግስት በሚመድበውና ወጪ በሚያደርገው በጀት ላይ በሂደቱ ቀጥተኛ ተሳታፊ እንዲሆኑ ማስቻል ነው።

2. ስለመንግስት በጀትና የበጀት አሰራር (አስተዳደር) ስርዓት

2.1. የመንግስት በጀት ምንነትና አስፈላጊነት

2.1.1. የመንግስት በጀት ስንል ምን ማለታችን ነው?

የመንግስት በጀት በአንድ የበጀት ዓመት (ከሐምሌ 1-ሰኔ 30) የሚፈጸም እና ስለ መንግስት ገቢና ወጪ የሚተነበይበት ሰነድ ሲሆን ይህም ሁሉም የመንግስት ባለበጀት መስሪያ ቤቶች ከተሰጣቸው ተግባርና ኃላፊነት አንጻር ሊያሳኩ ያስቀመጡትን ዓላማ እንዴትና በምን ያህል ሀብት እንደሚያከናውኑ በግልጽ የሚያሳይ ነው፡፡ የበጀት ሰነዱም በሚመለከተው በህግ-አውጭ አካል ከጸደቀ በኋላ ስራ ላይ ይውላል፡፡

2.1.2. የመንግስት በጀት ለሁለንተናዊ ልማት የሚጫወተው ቁልፍ ሚና

የመንግስት በጀት የፖሊሲ ማስፈጸሚያ መሣሪያ ነው። ይህ ማለት መንግስት የህዝቡን የልማትና መልካም አስተዳደር ጥያቄ ለመመለስ የሚወጥናቸውን ፕሮግራሞች/ፕሮጀክቶች ተግባራዊ

የሚያደርገውና የመንግስት አገልግሎቶችን ለህዝቡ የማቅረብ ኃላፊነቱን የሚወጣው በበጀት አማካኝነት ነው። በመንግስት የፖሊሲ ሰነዶች የተቀመጡ የህዝቡን የኑሮ ሁኔታ ለማሻሻል የተወጠኑ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ትልሞች ወይም ግቦች በበጀት ካልተደገፉ በተጨባጭ የማይታዩ የመንግስት ምኞቶች ሆነው ነው የሚቀሩት። ለዚህም ነው በመንግስት በጀት አስተዳደር ስርዓት ግልጽነትና ተጠያቂነት ለማስረጽ ከፍተኛ ርብርብ የሚደረገው።

2.1.3. የመንግስት በጀት ለምን ይዘጋጃል?

መንግስት የዜጎችን ፍላጎት ሁሉ በአንድ ጊዜ ለማሟት የሀብት ውስንነት ስላለበት ለዜጎች በቅድሚያ መቅረብ ያለባቸውን አገልግሎቶች በመለየትና ይህንንም ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችል ሀብት ከየትና እንዴት ሊገኝ እንደሚችል ለመወሰን በጀት ያዘጋጃል፡፡ በመሆኑም በበጀት ዝግጅት ቅድሚያ የተሰጣቸውና በበጀት የተደገፉ ተግባራት የመንግስትን ቁልፍ ስትራቴጂካዊ አቅጣጫዎችን የሚጠቁሙ ይሆናሉ ማለት ነው።

2.1.4. የመንግስት በጀት ዝግጅትና አፈጻጸም ሂደት

የመንግስት በጀት ዝግጅት ሂደት መነሻ የሚያደርገው የከተማ አስተዳደሩን የልማት ፖሊሲንና በዚሁ መነሻነት የሚዘጋጁ የልማት ፕሮግራሞች/ፕሮጀክቶች ሲሆን ሂደቱ በውስጣቸው በርካታ ተግባራትን ያካተቱ ደረጃዎችን (ዑደቶችን) ያካትታል። የመጀመሪያው የመካከለኛ ዘመን የፋይናንስ ዕቅድ (የሶስት አመት ተንከባላይ የወጪ ግምት) የሚዘጋጀበት (የዕቅድ ዑደት) ሲሆን ሁለተኛው ዓመታዊ በጀት የሚዘጋጅበት ሂደት (የበጀት ዑደት) ነው።

2.2. የመካከለኛ ዘመን የወጪ ማዕቀፍ ዝግጅት (የፋይናንስ ዕቅድ ዑደት)

የመካከለኛ ዘመን የወጪ ማዕቀፍ /Medium Term Expenditure Framework/ በመንግስት የልማት ፖሊሲዎች ፣ስትራቴጂዎች፣ ፕሮግራሞች፣ ፕሮጀክቶች እና በጀት መካከል ያለውን ትስስር በማጠናከር የልማት ፕሮግራሞችን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችል በየዓመቱ የሚታደስ የ3 ዓመት ተንከባላይ የወጪ ዕቅድ /Rolling plan/ ሲሆን ይህም የሀብት ምደባ፣ የወጪ ቁጥጥርና አጠቃላይ የመንግስት የፊስካል ፖሊሲ ውጤታማነትን ለማሻሻል እንዲሁም የሀብት ምደባን ከተጠያቂነት ጋር ለማስተሳሰር የሚረዳ ጠቃሚ የዕቅድ መሳሪያ ነው። ከዚህ ባሻገር የመካከለኛ ዘመን የወጪ ማዕቀፍ የፊስካል ተተንባይነትንና ግልጸኝነትን ስለሚያካትት መንግስት ፖሊሲዎችን ለማስፈጸም ያለውን ቁርጠኝነት ያንጸባርቃል።

የመካከለኛ ዘመን የወጪ ማዕቀፍ መሠረታዊ ዓላማ የበጀት ዝግጅት ከአንድ ዓመት ዕይታ ወደ መካከለኛ ዘመን ዕይታ በማሸጋገር፣ የመንግስትን የልማት ፖሊሲ የትኩረት አቅጣጫ መሠረት ባደረገ መልኩ ቅድሚያ ለሚሰጣቸው ዘርፎችና በየዘርፉ ለሚተገበሩ ፕሮግራሞች/ ፕሮጀክቶች እንዲመደብ በማድረግ እና የሀብት አቅርቦት ተተንባይነት በማሻሻል በመንግስት ፖሊሲ መካከል ትስስርን ከመፍጠር ባለፈ የሀብት አጠቃቀም ውጤታማነትን ማረጋገጥ ነው።

የመካከለኛ ዘመን የወጪ ማዕቀፍ ዝግጅት ሂደት ሁለት ዐብይ ተግባራትን የሚያካትት ሲሆን የመጀመሪያው በመካከለኛ ዘመን (ከ3-5 ዓመታት) የሚኖረውን የገቢና ወጪ መጠን ለመተንበይ ወሳኝ የሆኑ የማክሮኢኮኖሚ (አጠቃላይ የምርት ዕድገት፣ የዋጋ ግሽበት፣የስራ ዕድል ምጣኔ...) እና የፊስካል (የመንግስት የገቢና ወጪ ፖሊሲ) ታሳቢዎችን መተንተን ሲሆን ሁለተኛው ታሳቢዎቹን መሠረት በማድረግ የገቢ ትንበያ እና ቅድሚያ ለሚሰጣቸው የወጪ ፍላጎቶች ምደባ የሚካሄድበት ነው።

2.2.1. የበጀት ዑደት

በጀት የሚከተሉትን አራት ዑደት/ደረጃዎች ያካተተ ዑደት አለው።

(ሀ) በጀት ማዘጋጀት (Executive Preparation)

በአስፈጻሚው አካል የሚከናወነው የበጀት ዝግጅት የመጀመሪያው ደረጃ ሲሆን ይህም የከተማ ማዕከል መስሪያ ቤቶች፣የክፍለ ከተማ የድጎማ በጀት ማከፋፈያ ቀመር ማዘጋጀትን፣ የድጎማውን ግምት ማስታወቅን፣ የበጀት ጥሪ ማስተለለፍን፣ የበጀት ጥያቄ ማቅረብን፣ የተደገፈ በጀት ዝግጅትን እና የተደገፈ በጀት በካቢኔ ማጽደቅ የሚያካትት ነው።

(ለ) በሕግ አውጪ አካል ማጸደቅ (Legislative Approval) ፣

በህግ አውጪው (በከተማው ም/ቤት) የሚከናወነው በጀት የማጽደቅ ተግባር የበጀት ዑደት ሁለተኛው ደረጃ ሲሆን ይህም የሚከተሉትን ዋና ዋና ተግባራት የሚያካትት ነው።

- የክፍለ ከተማ የድጎማ በጀት ማከፋፈያ ቀመር ማጽደቅ፣
- የጸደቀውን በጀት አዋጅ ረቂቅ ማጽደቅ /ለምክር ቤቱ የተላከው በጀት በምክር ቤቱ የመንግስት ወጪ አስተዳደርና ቁጥጥር ኮሚቴ ተገምግሞ እንዲጸድቅ ለምክር ቤቱ ጉባኤ ይቀርባል፣
- የጸደቀውን በጀት ሥራ ላይ እንዲውል መፍቀድ /ምክር ቤቱም በጀቱን መርምሮ ያፀድቃል። በክፍለለ ከተማም ይህ ተግባር ተመሳሳይ ተግባራት ይከናወናል።


(ሐ) በአስፈፃሚ አካል ሥራ ላይ ማዋል (Executive Implementation)

ይህ የበጀት ዑደት ሦስተኛው ደረጃ ሲሆን በህግ አውጪው (በም/ቤት) የጸደቀው በጀት በአስፈጻሚው አማካኝነት ሥራ ላይ የሚውልበት ሲሆን ይህም የሚከተሉትን ሁለት ዐብይ ተግባራት ማለትም የታወጀውን በጀት ማስታወቅን እና የታወጀውን በጀት በሥራ ላይ ማዋልን ያካትታል፡-

(መ) ኦዲት እና ግምገማን (Audit)

ኦዲት በህግ አውጪው አካል የጸደቀው በጀት ለታለመለት ዓላማ በአግባቡ ጥቅም ላይ መዋሉን የማረጋገጥ ሥራ የሚከናወንበት የበጀት ዑደት የመጨረሻው (አራተኛው) ደረጃ ነው። ይህም ወጪዎች/ ክፍያዎች፣በጀት፣ ግዢ እና ንብረት አስተዳዳሩ በመንግስት ፋይናንስ አስተዳዳር፣ በመንግስት ግዢ አዋጅ እና የንብረት አስተዳዳር አዋጅ፣ ደንብ እና መመሪያዎች መሰረት ወጪው እና የንብረት አስተዳዳሩ መከናወን የማረጋገጥ ተግባር ነው።

ምስል 1፡ የበጀት ዑደት (Budget Cycle)



የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የ2019 በጀትም ከላይ በቀረበው ዑደት መሰረት የተዘጋጀ ነው።

2.2.2. የፋይናንስ የጊዜ ሠሌዳ

የፋይናንስ የጊዜ ሰሌዳ ማለት የፋይናንስ ዕቅድ ዝግጅትና የበጀት ሂደት መቼ ተጀምሮ መቼ እንደሚጠናቀቅ የሚያመለክት ሰነድ ነው። በሌላ አገላለጽ የፋይናንስ የጊዜ ሰሌዳ ከታች በሠንጠረዥ 1 በተገለጸው መሠረት በተራ ቁጥር 2 የተገለጸው የፋይናንስ ዕቅድ ዝግጅት እና በአራቱ የበጀት ዑደት ደረጃዎች የተካተቱት ተግባራት መቼና በማን እንደሚከናወኑ በዝርዝር የሚያሳይ መመሪያ ነው።

ሠንጠረዥ1፡ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የፋይናንስ የጊዜ ሰሌዳ

ተ.ቁ	ዑደት/ክፍል/ደረጃ	በኢትዮጵያ አቆጣጠር	ኃላፊነት የተሰጣቸው መ/ቤቶች
	የዕቅድ ዑደት/ደረጃ		
1	ከአንድ ዓመት በላይ የሆነ ዕቅድ	ሃምሌ1-ነሃሴ30	ፋይናንስ ቢሮ
2	ከአንድ ዓመት በላይ የሆነ ፕሮግራም	መስከረም15-ታህሳስ 30	ፋይናንስ ቢሮና የመንግስት መ/ቤቶች
3	ዓመታዊ የፋይናንስ ዕቅድ	ጳጉሜ1-ታህሳስ 30	ፋይናንስ ቢሮ
	የበጀት ዑደት ክፍል/ደረጃ/		
	ሀ.በአስፈጻሚ አካል የሚደረግ ዝግጅት		
1	የበጀት ዝግጅት	መስከረም21-መጋቢት7	የመንግሥት መ/ቤቶች
2	የክፍለ ከተማ የድጎማ በጀት ማከፋፈያ ቀመር ዝግጅት	መስከረም 20-ህዳር5	ፋይናንስ ቢሮ
3	የድጎማውን ግምት ማስታወቅ	ታህሳስ 30-ጥር 7	ፋይናንስ ቢሮ
4	የበጀት ጥሪ	ታህሳስ 30-ጥር 29	ፋይናንስ ቢሮና
5	የበጀት ጥያቄ	ጥር 30-መጋቢት 22	የመንግሥት መ/ቤቶች
6	የተደገፈ በጀት ዝግጅት	መጋቢት 23-ግንቦት 29	ፋይናንስ ቢሮ
7	የተደገፈ በጀት ማጽደቅ	ግንቦት 30-ሰኔ 13	ካቢኔ
	ለ.በህግ አውጪው መጽደቅ		
8	የክፍለ ከተማ የድጎማ በጀት ማከፋፈያ ቀመር ማጽደቅ	ህዳር 7-ታህሳስ 6	ካቢኔ
9	የጸደቀውን በጀት አዋጅ ረቂቅ ማጽደቅ	ሰኔ 14-ሰኔ 30	ምክር ቤት
10	የጸደቀውን በጀት ሥራ ላይ እንዲውል መፍቀድ	ሰኔ14-ሰኔ 30	ምክር ቤት
	ሐ.በአስፈጻሚ አካል ሥራ ላይ ማዋል		
11	የታወጀውን በጀት ማስታወቅ	ሃምሌ1-ሃምሌ 8	ፋይናንስ ቢሮ
12	የታወጀውን በጀት በሥራ ላይ ማዋል	ሃምሌ 9-ሰኔ 30 በሚቀጥለው በጀት ዓመት	የመንግሥት መ/ቤቶች

ምንጭ፡- የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳዳር የበጀት ማኑዋል 2006 ዓ.ም

3. ዜጎች በበጀት ዝግጅት ሂደት እንዴት ይሳተፋሉ?

የኢትዮጵያ ህገ-መንግስት እና የከተማ አስተዳደሩ ቻርተር ዜጎች በመንግስት ሁለንተናዊ ተግባራት ሙሉ ተሳትፎ እንዲያደርጉ ይደግፋል፡፡

- የኢፌዲሪ ህገ-መንግሰት በአንቀጽ 12 ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 እንደተገለጸዉ የመንግስት አሰራር ግልፅ በሆነ መንገድ መከናወን አለበት፡፡ ማንኛውም ኃላፊና የሕዝብ ተመራጭ

ኃላፊነቱን ሲያጎድል ተጠያቂ ይሆናል፡፡ በአንቀጽ 89 ንዑስ አንቀጽ 6 የሀገር ልማት ፖሊሲዎችና ፕሮግራሞች በሚዘጋጁበት ወቅት መንግስት ሕዝቡን በየደረጃው ማሳተፍ አለበት፡ ፡ የሕዝብንም የልማት እንቅስቃሴዎች መደገፍ አለበት፡፡

- የተሻሻለው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁጥር 361/1995 በአንቀጽ 7 ን/አንቀጽ 1 እና 3 ነዋሪዎች ስለከተማዉ የሚወሰኑ ጉዳዮችን በሚመለከት መረጃ የማግኘት፣ ሀሳብና ጥያቄ የማቅረብ እና መልስ የማግኘት መብት እንዳላቸዉ እንዲሁም የከተማዉ አስተዳደር ፖሊሲ፣ በጀት የሥራ ዕቅድና መመሪያ ለነዋሪዎች ይፋ መሆን እንዳለበት፣ በተመሳሳይም በአንቀጽ 59 ን/አንቀጽ 2 የከተማዉ በጀት በግልጽና ነዋሪዉን በሚያሳትፍ መልኩ መዘጋጀት እንዳለበት ይደነግጋል።
- በከተማ አስተዳደሩ የፋይናንስ ግልጽነትና ተጠያቂነት ስርዓት መተግበሪያ መመሪያ ቁጥር 05/2011 ክፍል አንድ ተራ ቁጥር 5 (1) እንደተገለጸዉ ሁሉም የመንግስት ባለበጀት መስሪያ ቤቶች የተሟላ፣ ቀላልና ወቅታዊ የሆነ የበጀት መረጃ ለዜጎች ማቅረብ ይኖርባቸዋል።

ምስል 2. ዜጎች በሚከተሉት መንገዶች በበጀት ሂደት ሊሳተፉ ይችላሉ፤



1. በተወካዮቻቸው አማካኝነት (On their representatives)

የህግ አውጪዉ/የህዝብ ተመራጮች አስፈጻሚዉን አካል በእቅድ ያቀረበዉን የወጪና የገቢ አሰባሰብ እንዲሁም እቅዱን ለማስፈጸም በሰጠዉ ውሳኔና የተገኘውን ዉጤት መነሻ በማድረግ በጥልቀት ሊመረምርና ኃላፊነቱን ባልተወጣ ጊዜ ተጠያቂ ያደርጋል፡፡



2. ቅድመ በጀት ውይይት(Pre-budget discussion)

- የቅድመ በጀት ውይይት- ህዝቡ የመንግስትን የወጪና የገቢ እቅድ እንዲያዉቅ በማድረግ የበጀት ዓመቱ በጀት ከመጽደቁ በፊት ለበጀት አፈጻጸም ዉጤታማነት ግብአት ሊሆኑ የሚችሉ ሀሳቦችን ከህዝቡ እንዲያገኝ እድል ይሰጣል፤
- የከተማዉ ምክር ቤት በአስፈጻሚ አካላት የቀረበለትን በጀት ከማጽደቁ በፊት የሲቪክ ማህበራት፤ ግለሰቦች፤ ተቋማትና ሌሎች የሚመለከታቸዉ አካላት በቀረበዉ ረቂቅ በጀት ላይ ሀሳብና አስተያየት እዲያቀርቡ በሚደረግ ሂደት ዜጎች መሳተፍ ይችላሉ፤



3. በመንግስት ተቋማት የህዝብ ተሳትፎ መድረኮች(public participation)

የመንግስት ባለበጀት መ/ቤቶች ከህብረተሰቡና ከሚመለከታቸዉ ባለድርሻ አካላት ጋር በተቋማቸው የሩብ አመትና ዓመታዊ የበጀትና እቅድ ዝግጅትና አፈጻጸም ግምገማ በሚደረግበት ወቅት ዜጎች መሳተፍ ይችላሉ፤



4. ማህበረሰብ አቀፍ የልማት ኮሚቴዎች (Community Based Development Committees)

በመንግስት አስፈጻሚ አካላትና በማህበረሰቡ ተነሳሽነት በተመረጡና በተቋቋሙ የልማት ኮሚቴዎች አማካኝነት ዜጎች ተሳታፊ ይሆናሉ፤



5. ሁለንተናዊ የዜጎች ተሳትፎ ስልቶች (Inclusive citizen participation strategies

የግልጽነትና ማህበራዊ ተጠያቂነት አሠራር ስርዓትን በህብረተሰቡ ዘንድ በማስረጽና የማህበረሰቡን አቅም በመገንባት፡

- ዜጎች የአገልግሎት አሰጣጥ ክፍተቶችን ይለያሉ። ይህን መሠረት በማድረግም ከአገልግሎት አሰጣጥ ጋር ተያይዘው የተለዩ የቅድሚያ ቅድሚያ ችግሮች ትኩረት እንዲያገኙ ለማድረግ የአገልግሎት ተጠቃሚው ማህበረሰብ በበጀት ዝግጅት ሂደት ላይ በንቃት ይሳተፋል።

በመሆኑም የከተማው አስተዳደር የ2019 በጀትም ከላይ በተገለፀው መሰረት ህብረተሰቡን በማሳተፍ ተዘጋጅቶ የቀረበ ነው።

4. የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የ2019 በጀት ዓመት በጀት

4.1. የከተማ አስተዳደሩ በጀት እንዴት ነው የሚዘጋጀው?

የከተማው አስተዳደር ከ2013 እስከ 2023 ዓ.ም ያለውን ጊዜ የሚሸፍን የአስር ዓመት ዕቅድ (ፍኖተ ብልጽግና) ከማዘጋጀቱም ባለፈ ለተግባራዊነቱ ሁለተኛው አምስት ዓመት (ከ2019 እስከ 2023) የልማት ፕሮግራም ነድፎ ከ2019 ዓ.ም ጀምሮ ተግባራዊ በማድረግ ላይ ይገኛል። በእነዚህ የረዥምና በመካከለኛ ጊዜ የልማት ዕቅድ ሰነዶች ውስጥ የተቀመጡት ግቦች ስኬት የሚወሰነው ለተፈጻሚነታቸው በሚመደበው በጀት መጠንና ውጤታማ አጠቃቀም ነው። ለዚህም ፖሊሲንና በጀትን ማስተሳሰርን መሠረት ያደረገ የበጀት ድልድል እና አጠቃቀም ስርዓትን መዘርጋት ወሳኝ ነው።

በዚህም መሠረት የከተማው ውስን ሀብት በከተማ አስተዳደሩ የረዥምና የመካከለኛ ጊዜ የልማት ፕሮግራሞች/ፕሮጀክቶች ቅድሚያ የተሰጣቸውን ግቦች ከማሳካት አኳያ የተቃኘና አጠቃቀሙም ተጠያቂነት ያለው እንዲሆን ለማድረግ የሚያስችል የ3 ዓመት ተንከባላይ የፋይናንስ ዕቅድ/ የመካከለኛ ዘመን የወጪ ማዕቀፍ / የመንግስት የበጀት አስተዳደር ስርዓት አካል ሆኖ ተግባራዊ እያደረገ ይገኛል።

የከተማ አስተዳደሩ ውስን የሆነውን የከተማዋን ሀብት ድልድል ከከተማዋ የልማት ፖሊሲ፣ ስትራቴጂ እና የትኩረት አቅጣጫዎች ጋር ይበልጥ ለማስተሳሰር የበጀት ዝግጅቱን ከአንድ ዓመት እይታ ወደ መካከለኛ ዘመን እይታ በማሸጋገርና አስተዳደሩ ቅድሚያ ለሚሰጣቸው ዘርፎች በመመደብ በየዘርፉ የሚተገበሩ ፕሮግራሞች ወጥነት እንዲኖራቸው በማድረግ አስፈላጊውን የመሰረተ ልማትና መሰረታዊ አገልግሎት በተፋጠነ ሁኔታ ለማቅረብ የሚያስችል ስርዓት የመዘርጋት ሂደት በተጠናከረ መልኩ በማካሄድ ላይ ይገኛል።

በዚህም-መሠረት የከተማው የ2019 በጀት ዓመት የበጀት ዝግጅት መነሻ ያደረገው የመካከለኛ ዘመን የወጪ ማዕቀፍ አካል የሆነውን የ3 ዓመት (የ2019-2021 በጀት ዓመት) የገቢና ወጪ ትንበያ ሲሆን ይህም የሚከተሉትን የማክሮ ኢኮኖሚና ፊስካል እንዲሁም አጠቃላይ ፖለቲካዊና ተቋማዊ ታሳቢዎችን መሠረት ያደረገ ነው።

- **የኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ ታሳቢዎች**
  - በሚቀጥሉት ሶስት ዓመታት (2019-2021) የከተማው አስተዳዳሩ ፈጣንና ቀጣይነት ያለው በቋሚ ገበያ ዋጋ በአማካይ 9.82% በላይ የኢኮኖሚ ዕድገት እንደሚያስመዘግብ እና ይህም በስራ እድል ፈጠራና በታክስ ገቢ ላይ አስተዋጽኦ እንደሚኖረው፣
  - እየታየ ያለው የዋጋ ግሽበት መንግስት በሚወስዳቸው የማክሮ ኢኮኖሚ እርምጃዎች እየቀነሰ እንደሚሄድና ዝቅተኛ ወይም መካከለኛ የዋጋ ግሽበት እንደሚኖር፣
  - አገራዊ የሰላም ሁኔታ ይበልጥ እየተጠናከረ እንደሚሄድ፣
- **የፊስካል ፖሊሲ እና የታክስ አስተዳደር ታሳቢዎች**
  - የፊስካል ፖሊሲ እና የታክስ አስተዳዳር ውጤታማ እንደሚሆን፣
  - በ2018 በጀት ዓመት በገቢ ዕቅድ አፈጻጸም የተገኙ ተሞክሮዎች ተጠናክረው እንደሚቀጥሉ፣

- እንደ አገር የተወሰዱ የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያዎች የፋይናንስ ተቋማትን የሚያጠናክር እና የውጭ ምንዛሬ አቅርቦትን እንደሚያሻሽለው፣
- ከታሪፍ፣ ከሎጂስቲክ አቅርቦት፣ ከኤሌክትሪክና ከቴሌኮም አገልግሎት ጋር በተያያዘ ለንግዱ ህብረተሰብ ማነቆ የሆኑ ተግዳሮቶችን እንደሚሻሻል፣
- ግብርን በታማኝነትና ህግን አክብሮ የመክፈል ባህል ይበልጥ እየጎለበተ እንደሚሄድ ፣
- በደንብ ቁጥር 184/2017 መሰረት በኢ-መደበኛ ንግድ የሚሳተፉ በርካታ የንግድ ድርጅቶች እና ግለሰቦችን ወደ መደበኛው ንግድር ስርዓት ለማምጣት እንደሚሰራ፣
- የመንግስት በጀት እና ወጪ አጠቃቀም (Budget Allocation & Government Spending) የከተማውን ምርታማነት በሚያሳድግ ላይ ትኩረት ተደርጎ እንደሚሰራ፣
- የመሰረተ-ልማት አቅርቦት ስራዎች ተጠናክረው እንደሚቀጥሉ እና የአምራች ኢንዱስትሪዎች እና አገልግሎት ዘርፉ እንደሚነቃቃ እና የውጭ ቀጥታ ኢንቨስመንት በተሻለ ሁኔታ እንደሚስብ፣
- በበጀት ዓመቱ በዕቅድ የተያዘው የታክስ ገቢ 100% እንደሚሰበሰብ፣
- የወጪ ቅነሳ በከተማው ስትራቴጂ ተይዞ ተግባራዊ እየተደረገ መሆኑ፣
- በከተማዋ ለቱሪዝም አቅም መሻሻል የተከናወኑ ተግባራት የጎብኝዎች ቆይታ እንደሚያሻሽለው እና በገቢም ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ እንደሚያሳድሩ ታሳቢ ተደርጓል።

4.2. ከ2019-2020 በጀት ዓመት የገቢ ትንበያ

ከላይ የተገለጹትን ታሳቢዎች ግምት ውስጥ በማስገባት የከተማው ገቢ ከታች በሰንጠረዥ2 እንደተመለከተው በ2019፣ 2020 እና 2021 እንደ ቅደም ተከተላቸው 39.49 %፣36.38% እና 37.42% ዕድገት እንደሚያሳይ ተተንብይዋል።

ሠንጠረዥ 2፡ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳዳር 2018 በጀት ዓመት የጸደቀ በጀት እና የ2019-2020 በጀት ዓመት የገቢ ትንበያ በቢሊየን ብር

ተ.ቁ	በጀት ዓመት	2018 የተስተካከለ በጀት አፈጻጸም እንደ መነሻ	2019	2020	2021
1	**የከተማ አስተዳደሩ የራስ ገቢ**	**337,483,897,789**	**488,510,942,571.00**	**671,617,483,179**	**925,656,848,159**
	የታክስ ገቢ	244,808,804,217.00	361,994,230,633.75	503,280,997,307.00	685,090,720,726.00
	ታክስ ያልሆኑ ገቢዎች	38,167,827,606.00	41,093,337,444.16	41,116,419,105.00	48,436,479,321.00
	ከማዘጋጃ ቤት የሚገኝ ገቢ	44,749,103,687.00	85,423,374,493.09	121,828,822,862.00	183,601,468,840.00
2	**የፌደራልመንግስት የበጀት ድጋፍ**	**22,404,264,490.00**	**13,763,975,584.000**	**15,396,974,194.00**	**19,710,687,907.00**
	ከመንገድ ፈንድ	-	2,639,418,388.00	2,000,000,000.00	4,000,000,000.00
	የውጭ አገር እርዳታ	1,474,936,542.00	1,773,872,363.00	1,848,110,465.00	2,009,949,128.00
	የውጭ/የአገር ውስጥ ብድር	11,171,165,668.00	9,350,684,833.00	11,548,863,729.00	13,700,738,779.00
	ጠቅላላ ድምር	**350,130,000,000.00**	**502,274,918,155.00**	**685,014,457,373.00**	**941,367,536,066.00**
	ዕድገት በብር	152,144,918,155.00	182,739,539,218.00	256,353,078,693.00	152,144,918,155.00
	ዕድገት በ%	**50.16%**	**39.49%**	**36.38%**	**37.42%**

ምንጭ፦ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፋይናንስ ቢሮ የመካከለኛ ዘመን የወጪ ማዕቀፍ 2018 ዓ.ም

ከላይ በሰንጠረዥ 2 ለማሳየት እንተሞከረው ምንም እንኳን ከተማችን የተለያዩ የገቢ ምንጮች ቢኖሯትም ከፍተኛውን ድርሻ 72.07% የሚይዘው የታክስ ገቢ ነው። በዚህም መሠረት የከተማዋን የኢኮኖሚ ዕድገት ከማስቀጠልና የነዋሪዎቿን የኑሮ ሁኔታ ከማሻሻል አኳያ ከታክስ የሚገኘው ገቢ የሚጫወተው ሚና ወሳኝነት አለው።

4.3. ከ2019-2021 በጀት ዓመት የወጪ ትንበያ

የከተማው ገቢ ከላይ በሠንጠረዥ 2 በተገለጸው ትንበያ መሠረት ዕድገት እንደሚያሳይ እና የሚከተሉት ታሳቢዎች እንደሚሟሉ ግምት ውስጥ ገብቷል።

- የከተማ አስተዳደሩ ራዕይ፣ ራዕዩን ለማሳካት የተነደፈው የ10 ዓመት ስትራቴጂክ ዕቅድ የትኩረት አቅጣጫና ከስትራቴጂክ ዕቅዱ በመነጨው የመጀመሪያው የአምስት የልማት ፕሮግራም ትኩረት የተሰጣቸው የልማትና መልካም አስተዳደር ግቦች፣
- ያለፉት 2 ዓመት (2016-2017) እና የ2018 የ11 ወራት የወጪ አፈጻጸም አዝማሚያ፣
- የከተማ አስተዳደሩ አስፈጻሚ አካላት የአደረጃጀት ለውጥና ይህም በወጪ ላይ ሊያስከትል የሚችለው ተጽእኖ፣
- የኮሪደር ልማት ቀጣይነት.
- የዋጋ ግሽበት እና የነዋሪው ህዝብ አዳዲስ የልማት ፍላጎቶች ዋና ዋናዎቹ ናቸው።

ሠንጠረዥ3 ፡ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳዳር የ3 ዓመት (2019-2021 በጀት ዓመት) የወጪ ትንበያ

ወጪ	2018 አፈጻጸም (መነሻ ዓመት)	2019	2020	2021
የከተማው አጠቃላይ ወጪ በቢሊየን ብር	349.13	502.27	685.01	941.37
መደበኛ ወጪ በቢሊየን ብር	101.25	145.66	198.65	273
ዕድገት %		12.72%	10.55%	10.85%
ካፒታል ወጪ በቢሊየን ብር	247.88	356.61	486.36	668.37
ዕድገት %		43.86%	36.38%	37.42%
የካፒታል ወጪ ከአጠቃላይ ወጪ የሚኖረው ድርሻ (በመቶኛ)	71%	71.53%	71.53%	71.53%

ምንጭ፦የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፋይናንስ ቢሮ የመካከለኛ ዘመን የወጪ ማዕቀፍ 2018 ዓ.ም

4.4. የከተማው አስተዳደር ለ2019 በጀት ዓመት የጸደቀ በጀት

የከተማው የ2019 የጸደቀ በጀት ብር 502.27 ቢሊየን ሲሆን ከዚህ ውስጥ ለመደበኛ ብር 145.66 ቢሊየን እና ካፒታል 356.61 ቢሊየን ተደልድሏል።

ከአጠቃላይ ዓመታዊ በጀት ውስጥ ለማዕከል መስሪያ ቤቶች ብር 398.13 ቢሊየን ሲሆን ቀሪው ብር 104.15 ቢሊየን ለክ/ከተሞችና በሥራቸው ለሚገኙ ወረዳዎች የተመደበና በቀመር የተከፋፈለ ነው።

የ2019 የከተማው በጀት ዕድገት አዝማሚያ ሲታይ ካለፈው 2018 በጀት ዓመት ብር 152.14

ቢሊየን ወይም 39.49 በመቶ ዕድገት አለው። የካፒታል በጀት ከፍተኛ ዕድገት ያሳየበት ምክንያት በኮሪደር ልማት የተጀመሩ ነባር ፕሮጀክቶች እና የከተማው አስተዳዳር የትኩረት አቅጣጫን መሰረት ያደረጉ የካፒታል ፕሮጀክቶች ከግምት ውስጥ ገብተው በጀት እንዲደገፍላቸው በመደረጉ ነው።

4.5. የከተማ አስተዳደሩ የገቢ በጀት ምንጮች

ሁሉም ክልሎች እና የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር ከፌዴራል መንግስት በየዓመቱ ድጎማ በቀመር የሚያገኙ ሲሆን አዲስ አበባ ከተማ አስተዳዳር ግን ምንም ዓይነት ድጎማ የማታገኝና የራሷን ወጪ ከተማዋ ከምታመነጨው ሀብት የምትሸፍን ብቸኛ ከተማ ነች። የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በተሻሻለው የከተማው ማቋቋሚያ ቻርተር ቁጥር 361/1995 መሰረት

1. **ታክስ ገቢ/Tax Revenue / ቀጥታ ታክስ** /Direct Taxes/ የግለሰብ ገቢ ግብር፣ የኪራይ ገቢ፣ የንግድ ትርፍ ገቢ ግብር፣ ዊዝ ሆልድ ታክስ.... / እና ቀጥታ ካልሆኑ ታክስ/ Indirect Taxes/ተጨማሪ እሴት ታክስ፣ ኤክሳይዝ ታክስ፣ ተርን ኦቨር ታክስ፣
2. **ታክስ ያልሆኑ ገቢዎች** / Administrative fees and charges, Sales of Public Goods and Services/
3. **ማዘጋጃቤታዊ ታክስ ገቢ**/Municipal Taxes/ማዘጋጃቤታዊ ታክስ እና ማዘጋጃቤታዊ አገልግሎቶች
4. **የመንገድ ፈንድ-** /Road Fund/
5. **ዕርዳታ** /ከልማት አጋሮች ለመሠረታዊ አገልግሎቶች ለትምህርት ፣ ለጤና ...የሚገኝ /
6. **ብድር** /በተለይ ለውሃ፣ለመንገድ እና ትራንስፖርት / ናቸው።

4.6. የከተማ አስተዳደሩ የ2019 የበጀት ድልድል

4.6.1. የበጀት ድልድል ስርዓት

የከተማው አስተዳዳር በጀት የሚደለድልበት ስርዓት መነሻው የተሻሻለው የከተማው አስተዳዳር ማቋቋሚያ ቻርተር አዋጅ ቁጥር 361/1995 እና የተሻሻለው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳዳር የፋይናንስ አስተዳዳር አዋጅ ቁጥር 51/2009 ነው።

በዚህ መሰረት በከተማ አስተዳዳሩ የጸደቀ የመካከለኛ ዘመን የወጪ ማዕቀፍ መነሻ በማድረግ ዓመታዊ የበጀት መመሪያ ይዘጋጃል። መመሪያው የሚያገለግለው ለቀጣይ በጀት ዓመት ብቻ ሆኖ በማክሮ-ኢኮኖሚና ፊስካል ማዕቀፍ/ MTEF/ ውስጥ የተቀመጡ ከሀብት አሰባሰብ እና ከወጪ አመዳደብና አጠቃቀም ጋር ያሉትን ዋና ዋና ጉዳዩችን ያካትታል።

4.6.2. ለማዕከል ባለበጀት ተቋማት የተመደበ በጀት

በከተማ ደረጃ ለሚገኙ የማዕከል መ/ቤቶች ለ2019 በጀት ዓመት ጠቅላላ ብር 398.13 ቢሊየን የጸደቀ ሲሆን ከዚህ ውስጥ ለመደበኛ ብር **69.18 ቢሊየን/ ለደመወዝ** 23.69 ቢሊየን ፣ ለስራ ማስኬጃ 29.491 ቢሊዮን፣ 16.00 ለመጠባበቂያ/ እና ለካፒታል ብር 328.95 ቢሊየን ተደልድሏል።

4.6.3. የክ/ከተሞችና ወረዳዎች በጀት ድጋፍ (ድጎማ)

የክፍለ ከተሞች የ2019 በጀት ዓመት ጠቅላላ የተመደበ በጀት ብር 104.15 ቢሊየን የተደለደለ ሲሆን ከዚህ ውስጥ ለመደበኛ በጀት ብር 73.79 ቢሊየን እና ለካፒታል ደግሞ ብር 30.35 ቢሊየን በመሆን ተደልድሏል። ለክፍለ ከተሞች ከተመደበው ጠቅላላ የካፒታል በጀት ውስጥ ብር 22.768 ቢሊየን የሚሆነው በዓላማ የተገደበ (ተለይተው ለተቀመጡ ፕሮጀክቶች/ፕሮግራሞች ማስፈጸሚያ የሚውል) በጀት ሲሆን ቀሪው ብር 7.589 ቢሊየን በዓላማ ያልተገደበ (በክ/ከተሞች ውሳኔ መሠረት ቅድሚያ ለሚሰጣቸው ፕሮጀክቶች የሚውል) በጀት ነው።

ሠንጠረዥ 4፡-የ2019 በጀት ዓመት የተፈቀደ ወጪ ዕቅድ እና ከአጠቃላይ ያለው ድርሻ

ተ.ቁ	የበጀት ዓይነት	የወጪ ዕቅድ (ቢሊየን ብር)	ከአጠቃላይ ያለው ድርሻ (%)
1	ጠቅላላ በጀት	502,274,622,540.00	100.00
2	በማዕከል የከተማ አስተዳደሩ አስፈጻሚ አካላት	398,125,991,796.00	79.26
2.1	ለመደበኛ ወጪ	69,178,884,456.00	17.38
2.1.1	ለደመወዝ	23,687,548,380.00	34.24
2.1.2	ለሥራ ማስኬጃ	29,491,336,076.00	42.63
2.1.3	ለመጠባበቂያ	16,000,000,000.00	54.25
2.2	ለካፒታል ወጪ	328,947,107,340.00	82.62
3	ለክ/ከተሞች የሚከፋፈል የበጀት ድጋፍ (ድጎማ)	104,148,630,744.00	20.74
3.1	መደበኛ ወጪ	73,790,971,425.00	70.85
3.1.1	ደመወዝ	44,274,582,860.00	42.51
3.1.2	ስራ ማስኬጃ	26,925,908,120.00	25.85
3.1.3	መጠባበቂያ	2,590,480,448.00	2.49
3.2	ካፒታል ወጪ	30,357,659,319.00	29.15
3.2.1	ጥቅል (በዓላማ ያልተገደበ) ድጋፍ	7,589,414,829.75	25.00
3.2.2	በዓላማ የተገደበ የበጀት ድጋፍ	22,768,244,489.25	75.00

ምንጭ፦ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፋይናንስ ቢሮ 2018 ዓ.ም

4.4.4. የ2019 የጸደቀ በጀት በዘርፍ


ከታች በሰንጠረዥ 5 ላይ እንደተመለከተው በ2019 በጀት ዓመት ከጸደቀ በጀት ውስጥ ከፍተኛው በጀት የተመደበው ለኢኮኖሚ ዘርፍ ብር 237.34 /47.252%/ ሲሆን አስተዳደራዊና ጠቅላላ አገልግሎት ብር 121.34 /24.159%/፣ ማህበራዊ ብር 81.36/16.2%፣ማዘጋጃቤታዊ ብር 37.75 /7.517%/ እና ሌሎች 24.47/4.872 %/ ድርሻቸውን ይወስዳሉ።

ሠንጠረዥ 5 ፡- የ2019 በጀት ዓመት የጸደ በጀት በዘርፍ (በቢሊየን ብር)

ዘርፍ	የጸደቀ በጀት	ድርሻ (በመቶኛ)
አስተዳዳርና ጠቅላላ አገልግሎት	121.34	24.16%
ኢኮኖሚ	237.34	47.25%
ማህበራዊ	81.37	16.20%
ሌሎች	24.47	4.87%
ማዘጋጃቤታዊ	37.76	7.52%
ጠቅላላ ድምር	502.27	100%

ምንጭ፡- የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳዳር ፋይናንስ ቢሮ 2018 ዓ.ም

ግራፍ 1. የ2019 በጀት ዓመት የጸደቀ በጀት የዘርፍ ድርሻ በመቶኛ/%/




ምንጭ፡- የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳዳር ፋይናንስ ቢሮ 2018 ዓ.ም

4.6.4. በወጪ ዕቅድ ትኩረት የተሰጣቸው ሴክተሮች/ዘርፎች

የከተማ አስተዳዳሩ የ10 ዓመት ስትራቴጂክ ዕቅድ ለድህነትና የዜጎችን ቅድመ ፍላጎቶች መሰረት በማድረግ የከተማ አስተዳዳሩ በጀት በዋናነት ለዘላቂ ልማትና ድህነት ተኮር ዘርፎች ላይ ያተኮረ ሲሆን በተለይም በመሰረተ ልማት ግንባታ፣በውሃና ፍሳሽ፣ጤና፣ትምህርት ፣ስራ ዕድል ፈጠራ፣ የመኖሪያ ቤትና ትራንስፖርት፣ለአካባቢ ጥበቃ ፣ለቴክኖሎጂ ልማት ፣ለጽዳት እና በሴቶችና ህጻናት ዘርፍ ላይ በማተኮር ሀገራችን ለማሳካት የገባችውን የዘላቂ የልማት ግቦችን ማዕከል ያደረገ ነው።

በዚህ መሰረት የዜጎችን ቅድመ ፍላጎቶች መሰረት በማድረግ ከአጠቃላይ ለ2019 ብር 502.27 ቢሊየን ውስጥ 360.86 ቢሊየን ወይም 71.84 በመቶ የ10 ዓመት ፍኖተ-ብልጽግና እና የቀጣይ 5 ዓመት የልማት ዕቅድ ላይ የተመለከቱ የትኩረት አቅጣጫዎችንና ስትራቴጂክ ግቦችን ለማሳካት የሚያስችል ለ11 ዘርፎች የተመደበ ሲሆን መሰረት ባደረገ መልኩ ነው። በዚህም መሰረት ለግንባታ ዘርፍ ብር 71.11 ቢሊየን (14.16%) ፣ ለመንገድ ልማት ዘርፍ 45.16 ቢሊየን (8.99%)፣ ለውሃና ፍሳሽና ጽዳት ዘርፍ ብር 44.97 ቢሊየን (8.95%)፣ ለትምህርትና ስልጠና ዘርፍ ብር 35.4 ቢሊየን (7.05%)፣ለጤና ዘርፍ ብር 34.95 ቢሊየን (6.96%) ፣ ለቤቶች ልማት ዘርፍ ብር 34.22 ቢሊየን (6.81%) ፣ ለትራንስፖርት ዘርፍ ብር 27.40 (5.46%) ፣ለመሬት ልማትና አስተዳደር ዘርፍ ብር 21.14 ቢሊየን (4.21%) ፣ ለአካባቢ ጥበቃ እና አረንጓዴ ልማት ዘርፍ 20.83 ቢሊየን (4.15%) ፣ ለሰላምና ጸጥታ ዘርፍ ብር 13.18 ቢሊየን (2.62%) ፣ ሴቶች ህጻናት ወጣቶችና ማህበራዊ ዘርፍ ብር 12.47 ቢሊየን(2.48%) ለአብነት መጥቀስ ይቻላል።

ግራፍ 2 በበጀት ምደባ ወቅት ትኩረት የተሰጣቸው ዘርፎች ከአጠቃላይ በጀት ያላቸው ድርሻ በመቶኛ



ምንጭ፡- የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳዳር ፋይናንስ IBEX ሪፖርት 2018 ዓ.ም

4.6.5. ልዩ ትኩረት የተሰጣቸውና ከፍተኛ በጀት የተመደበላቸው ድህነት ተኮር ፕሮግራሞች

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳዳር የበጀት ድልድሉ በዋናነት ድህነት ተኮር ዘርፎች ላይ ቢሆንም የህብረተሰቡን ኑሮ፣የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴ እንዲሁም ከዚህ ጋር ተያይዞ የሚፈጠረውን የስራ ዕድል ከግምት ውስጥ በማስገባት ከዚህ በታች ለቀረቡት ፕሮግራሞች ልዩ ትኩረት እንዲሰጥ ተደርጓል።

4.6.5.1. የከተማ ልማታዊ ሴፍቲኔት እና ስራ ፈጠራ

ዜጎች ምርታማ እንዲሆኑና ከድህነት እንዲላቀቁ በመንግስት እና በዓለም ባንክ በጥምረት ባለፉት አምስት ዓመታት የነበረው የከተማ ምግብ ዋስትና ከድህነት ወለል በታች በሚገኙ የከተማ ነዋሪዎችን እሴት በሚጨምሩ የአካባቢ ልማት ስራዎች ተጠቃሚ ተደርገዋል። በዚህ መሰረት በያዝነው 2019 በጀት ዓመት ደግሞ በቀጥታ ድጋፍ /ብር 962.78 ሚ /፣ለወጣቶች ክህሎት ስልጠና /ብር 1.20 ቢ /፣ በልማት ስራዎች / ብር 3.98 ቢ / እና ለአስተዳዳር ስራዎች/ብር 188.48 ሚ/በአጠቃላይ 346,338 ተጠቃሚዎች ብር 6.33 ቢ በጀት ተይዟል።

4.6.5.2. ማህበራዊ ተጠያቂነት ፕሮግራም (ESAP)

ፕሮግራሙ የዜጎችን የልማት ተሳትፎ በማሳደግ ጠያቂ፣ ሞጋችና ችግር ፈቺ ማህበረሰብን መፍጠር ሲሆን ይህም አሠራር በኢትዮጵያ ማህበራዊ ተጠያቂነት ፕሮግራም አማካይነት በሁሉም ክፍለ ከተሞችና በተመረጡ 11 ሞዴል ወረዳዎች ተግባራዊ እየተደረገ የሚገኝ ሃገራዊ የመልካም አስተዳደር ፕሮግራም አካል ነው፡፡ በያዝነው 2019 በጀት ዓመት ደግሞ በ9 ክፍለ ከተሞች 16 ወረዳዎች 16 ትምህርት ቤቶች ላይ ወረዳዎች ተግባራዊ ይደረጋል።

ፕሮግራሙ ተግባራዊ በሚደረግባቸው ወረዳዎች በ2019 ዓ.ም የአገልግሎት ተጠቃሚው ማህበረሰብ በራሱ የለያቸውን አንገብጋቢ የአገልግሎት አቅርቦት ችግሮች ምላሽ ለመስጠት በተለይ ከትምህርት ጋር ተያይዞ ለተነሱ አዳዲስ የመማሪያ ክፍሎች ግንባታና ማስፋፊያ፣ የመመገቢያ አዳራሾች፣ የአስተዳደር ህንፃ፣ መጸዳጃ ቤት የትምህርት ቤት አጥር፣ ምድረ ግቢ ምቹነት፣የስፖርት ማዘውተሪያ ሜዳ፣ የመማር ማስተማር ግብዓቶች ማሟያ...ወዘተ) ፕሮጀክቶች የሚውል አስተዳደሩ በ2019 በጀት ዓመት 2.23 ቢሊየን ነው።

4.6.5.3. የተማሪዎች ምገባና የተለያዩ ድጋፎች

በ2012 ዓ.ም ለ382,410 ተማሪዎች ምገባ እና ደንብ ልብስ ድጋፍ መርሃ ግብር የተጀመረ ሲሆን በያዝነው 2019 በጀት ዓመት 608,751 በላይ ለሚሆኑ ተማሪዎች ለምገባ መርሀግብር ብር 5.28 ቢሊየን ለደንብ ልብስ ደግሞ ብር 2.22 ቢሊየን ተመድቦ ወደ ተግባር ተገብቷል። በአጠቃላይ ለምገባ እና ለተለያዩ ድጋፎች በበጀት ዓመቱ ብር 7.5 ቢሊየን የተበጀተ ሲሆን አስተዳደሩ ለዘርፉ ትኩረት መስጠቱን ያመላክታል።

4.6.5.4. የአዲስ አበባ የከተማ አውቶቡስ አገልግሎት ድርጅት

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳዳር የትራንስፖርት አገልግሎቱን ተገልጋዩ ቀልጣፋ አገልግሎት እንዲያገኝ የሚያደርጋቸው ኢንቨስትመቶች እንደተጠበቁ ሆነው ነዋሪው ህዝብ አገልግሎቶችን ኪሱን በማይጎዳና የኑሮ ጫናው እንዳያማርረው ታሳቢ ባደረገ መልኩ አገልግሎት እንዲያገኝ በመንገደኞች ቲኬት ላይ ድጎማ ሲያደርግ ቆይቷል። በዚሁ መሰረት የመንገደኞች ቲኬት ድጎማን በያዝነው 2019 በጀት ዓመት ብር 2.5 ቢሊየን ብር በላይ ለዚህ ተግባር በጀት ተይዟል።

4.6.5.5. ፐብሊክ ሰርቪስ ሰርቪስ ትራንስፖርት አገልግሎት

ለፐብሊክ ሰርቪስ ሰራተኛም የትራንስፖርት ችግርን በማቃለል ምርታማነታቸውንና አገልግሎት አሰጣጥን ለማሻሻል በ2018 በጀት ዓመት ብር 1.038 ቢሊየን ወጪ የተደረገ ሲሆን በ2019 በጀት ዓመት በተመሳሳይ ደግሞ ብር 1.038 ቢሊየን ለዚህ ተግባር በጀት ተይዟል።

4.6.5.6. አዲስ አበባ ቀላል ባቡር አገልግሎት

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳዳር የትራንስፖርት አገልግሎቶችን አቅርቦትንና ተደራሽነትን ለማሻሻል ከኢትዮጵያ ምድር ባቡር ኮርፖሬሽን የአዲስ አበባ ቀላል ባቡርን የተረከበ በ2018 በጀት ዓመት ዘርፉን ውጤታማ ከማድረግ አንጻር ብር 500 ሚሊየን በጀት ተይዞ የነበረ ሲሆን በ2019 በጀትም በተመሳሳይ ለዚህ ተግባር ብር 500 ሚሊየን መድቦ ወደ ተግባር ተብቷል።

4.6.5.7. ብርሃን ዳቦ ድጎማ

የከተማ አስተዳዳሩ ነዋሪው ህብረተሰብ በኑሮ ውድነት ምክንያት የሚታየውን ጫና ለመቀነስ ለሸገር ዳቦ አቅርቦትን በዝቅተኛ ዋጋ እንዲቀርብ ለመደጎም በመቶ ሚሊየን ብር ድጎማ አድርጓል። ባለፈው 2018 በጀት ዓመት 492 ሚሊዮን ተይዞ የነበረ ሲሆን በ2019 በጀት ዓመት ደግሞ በተመሳሳይ ለዚሁ ተግባር 492 ሚሊየን ብር ድጋፍ በጀት እንዲያዝ ተደርጓል።

4.7. ገቢን ከማሳደግና ወጪን ከመቆጠብ አኳያ የተወሰዱ አዳዲስ የፖሊሲ እርምጃዎች

ባለፉት ሶስት ዓመታት(2016-2018) የከተማ አስተዳዳሩ የፊስካል ፖሊሲ ውጤታና ወጪ ቆጣቢ በማድረግ ገቢን ለማሳደግ ከተወሰዱ እርምጃዎች መካከል የመንግስት መስሪያ ቤቶች አገልግሎት ክፍያ ማሻሻያ፣ የቤት ግብር ገቢ፣ የቤት ሽያጭ ገቢ ግብር በዋነኝነት የሚጠቀሱ ሲሆን በአንጻሩ የወጪ ቅነሳ መመሪያ ማውጣት፣ ወጪን በኖርም መገደብ እና የቢሮ ኪራይ ወጪን ለመቀነስ የአስፈጻሚ ተቋማት የቢሮ አደረጃጀት በማዕከል ማድረግ ወጪን ከመቆጠብ ጋር በተያያዘ ከተወሰዱ እርምጃዎች ውስጥ የሚጠቀሱ ናቸው።

በ2019 በጀት ዓመትም ገቢን ለማሳደግና ወጪን ለመቀነስ የሚደረገው ጥረት በተጠናከረ መልኩ የሚቀጥል ሲሆን በዚህም መሠረት የሚከተሉትን እርምጃዎች ለመውሰድ ታቅዷል፡-

- የቤት ግብር ገቢ እና የቤት ሽያጭ ገቢ ግብር በተጠናከረ መልኩ ተግባራዊ ማድረግ
- የመንግስት አገልግሎት ክፍያ ተመን ማሻሻያ፣
- የኪራይ ገቢ ግብር ማስፈጸም፣
- የታክስ ገቢንና ስጋትን በጋራ ለመከላከል የሚያስችል ተግባራት እንደሚሰሩ፣

ወጪን ከመቀነስ አንጻር

- የኤሌክትሪክ ተሽከርካሪዎች ግዢና ወደ አገልግሎት በስፋት ማስገባት፣
- የከተማ አስፈጻሚ አካሎች አደረጃጀት ጥናትና ትግበራ፣
- እሴት የማይጨምሩ ወጪዎች እንዲቀንሱና እንዲታጠፉ መስራት፣
- የከተማ አስተዳዳሩን የልማት ፍላጎት ምላሽ ለመስጠት፣

የበጀትና ፋይናንስ ቴክኒካል ቃላቶችና ሀረጎች መግለጫ

1) **የአስተዳደር** ስልጣን:- በመንግስት አስተዳደር ከከተማ አስተዳዳር እስከ ወረዳ ድረስ ያለው የስልጣን ተዋረድ ማለት ነው፡፡
2) የበጀት ዑደት፡- በመንግስት በጀት አስተዳዳር ስርዓት ውስጥ የሚካተቱ ዋና ዋና ተግባራትን በጀት ማዘጋጀት፣ማጸደቅ፣ሥራ ላይ ማዋል እና አዲት እና ግምገማ በቅደም ተከተል/በደረጃ የሚያመለክት ነው።
3) የበጀት ጥሪ፡- በፋይናንስ ቢሮ የተዘጋጀና ባለበጀት መ/ቤቶችም በተቀመጠው የበጀት ማዘጋጃ መመሪያ መሰረት ለመ/ቤታቸው እቅድ ማስፈፀሚያ የሚያስፈልጋቸውን በጀት አዘጋጅተው እንዲቀርቡ ማሳሰብ ነው።
4) የበጀት ጥያቄ፡- የመንግስት ተቋማት ከፋይናንስ ቢሮ በተላለፋቸው የበጀት ጥሪ መሰረት ያስፈልገኛል ያለውን የበጀት አመቱን የወጪ አይነት በዝርዝር ለፋይናንስ ቢሮ የሚያቀርበው ጥያቄ ነው፡፡
5) የበጀት ድጎማ፡- የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳዳር ለተቋማት/ክፍለ ከተሞች የሚሰጠውን የበጀት ድጋፍ ነው።
6) **የካፒታል ወጪ፡-** በተቋማት የመንግስትን አገልግሎት ለመስጠትና ለማሻሻል ቋሚ ሀብት ለማፍራት ወይንም ለማሻሻል የሚውል ወጪ ነው፡፡
7) የዜጎች በጀት፡- መሠረታዊ የበጀት መረጃዎች ዜጎች ሊረዱት በሚችሉ ቀላል እና ግልፅ በሆነ ቋንቋ ተዘጋጅቶ ለሁሉም ተደራሽ የሚደረግ የበጀት መረጃ ሰነድ ነው።
8) የዜጎች ሁለንተናዊ ተሳትፎ፡- ከመንግስት የሚሰጡ የመሰረታዊ አገልግሎቶች ለማሻሻል ዜጎች በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ በእቅድ ዝግጅት፣ ትግበራና የአፈፈፃፀም ግምገማ ላይ የሚያደርጉትን ሁለንተናዊ ተሳትፎን ያመለክታል፡፡
9) የከተማ አስተዳደሩ የራስ ገቢ፡- መንግስት የበጀት ዓመቱን ወጪ ለመሸፈን ከሀገር ውስጥ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ከታክስ፣ ታክስ ካልሆኑ እና ማዘጋጃቤታዊ ገቢዎች የሚሰበስበው የሚያመለክት ነው።
10) የኢኮኖሚ መረጋጋት፡- የማክሮ ኢኮኖሚው ከመጠን በላይ አለመለዋወጥና በተከታታይነት የማያቋርጥ የዕድገት መጠን፣ ዝቅተኛ እና የተረጋጋ የዋጋ ግሽበት ያለው ኢኮኖሚ ማለት ነው።
11) የውጭ እርዳታ፡- በመንግስት አቅም ሊሸፈኑ የማይችሉትን መሰረታዊ አገልግሎቶችን ለመደገፍና ለማገዝ ከሚፈልጉ የውጭ መንግስታትና እርዳታ ድርጅቶች የሚገኝ ሀብትን የሚያጠቃልል ሲሆን በዚህ ሰነድ አውድ የፌደራል መንግስት ከላይ በተገለጸው መልኩ ከሚያገኘው ሀብት ለከተማ አስተዳደሩ የሚመድበውን ድርሻ ያመለክታል።
12) የውጭ ብድር፡- መንግስት የወጪ ግዴታውን ለመወጣት የሚያስፈልገውን ሀብት ከሀገር ውስጥ ከሚገኝ የበጀት ምንጭ መሸፈን በማይችልበት ሁኔታ የበጀት ጉድለቱን ለማሟላት ከውጭ አበዳሪዎች የሚገኘውን ሀብት ሲሆን በዚህ ሰነድ ዐውድ የፌደራል መንግስት ከላይ በተገለጸው አግባብ ከሚያገኘው ሀብት ለከተማ አስተዳደሩ የሚመድበውን ድርሻ ያመለክታል።
13) የበጀት ዓመት፡- በመላ ሀገሪቱ ወጥ የሆነና በኢትዮጵያ ዘመን አቆጣጠር መሰረት ከሐምሌ 1 እስከ ሰኔ 30 ድረስ ያሉትን 12 ወራት የሚሸፍን የበጀት ትግበራ ጊዜ ማለት ነው።

14) የፊስካል ፖሊሲ፡- መንግስት ኢኮኖሚውን ለመቆጣጠር የመንግስት ገቢ አሰባሰብና ወጪ አደረራረግ የሚመራበት ስርዓት ነው።
15) የፋይናንስ ሀብት/ገቢ፡- መንግስት ለሚሰጠው አገልግሎት የሚውሉ ወጪዎችን ለመሸፈን ከታክስ፣ ታክስ ካልሆኑና ከሌሎች የገቢ ምንጮች የሚገኘው ገንዘብ ማለት ነው።
16) የመካከለኛ ጊዜ የወጪ ማዕቀፍ፡- የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳዳር የሦስት ዓመት የወጪ ዕቅዶችን ያወጣል፡ በጀቶች የመንግስትን ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ቅድሚያ የሚሰጣቸውን የሚያንፀባርቁ እና ለመንግስት መልሶ ግንባታ እና ልማት ግዴታዎች ተግባራዊ እንዲሆኑ ለማድረግ ያለመ ነው።
17) ጥቅል የሀገር ውስጥ ምርት፡- በአንድ የተወሰነ ጊዜ ውስጥ በአንድ ሀገር ውስጥ የተደረጉ ከሁሉም ከተጠናቀቁ ምርትና አገልግሎቶች የተገኘ የገንዘብ ዋጋ ነው።
18) የዋጋ ግሽበት/ንረት መጠን፡- አሁን ያለውን የሸቀጦትና አገልግሎቶች ዋጋ ከዚህ በፊት ከነበረው ዋጋ ጋር በማነጻጸር የዋጋ ለውጡን በመቶኛ መስቀመጥ ነው።
19) ማክሮ ኢኮኖሚ፡- የአጠቃላይ ወይም ጥቅል ሀገራዊ ኢኮኖሚው አወቃቀር፣ አፈፃፀም፣ ባህሪንና የውሳኔ አሰጣጡን የሚያመለክት ነው፡፡
20) የማክሮ ኢኮኖሚና ፊስካል ማዕቀፍ፡- አመታዊ የፊዝካል ዕቅዶችና ግቦች የፖሊሲ ትግበራ አማራጮች የሚወሰኑበት እንዲሁም ተግባራዊ ሊሆን የሚችል የበጀት ዓመቱ የገቢና ወጪ ግምት የሚከናወንበት ማዕቀፍ ነው፡፡
21) ፖሊሲ፡- በሚመለከታቸው የመንግስት አካላት ስምምነት ላይ የተደረሰባቸውና ሊተገበሩ የታቀዱ ውጥኖች ማስፈፈፀሚያ መመሪያ ነው።
22) ቅድመ-በጀት ውይይት፡- በወረዳ ደረጃ የዜጎችን የመሰረታዊ አገልግሎቶች ቅድመ-ፍላጎቶችና ምርጫዎች በዕቀድ ለማካተትና ለማከናወን ከወረዳው የተለያዩ የማህበረሰበ ክፍሎች ከተወከሉ ነዋሪዎች ጋር የሚደረግ ውይይት ነው፡፡
23) ቅድመ-በጀት መግለጫ፡- በበጀት ዓመቱ በመንግስት አስፈጻሚ አካላት የሚዘጋጀዉ የበጀት ፕሮፖዛል ለህግ አዉጭዉ አካል (የከተማዉ ም/ቤት) ቀርቦ ከመጽደቁ በፊት አስፈጻሚዉ አካል ባቀረበዉ ረቂቅ ላይ ውይይትና ክርክር የሚያድርግበት እንዲሁም ሌሎች የሚመለከታቸው የማህበረሰብ ተወካዮች፣ ተቋማትና ግለሰቦች አስተያየት የሚሰጡበት እና በዚህም መሠረት ማስተካከያ የሚደረግበት መግለጫ ነው፡፡
24) የመንግስት ተቋማት (የመንግስት ባለበጀት መ/ቤቶች)፡- በከተማ አስተዳደሩ በአዋጅ የተቋቋመና ሙሉ በሙሉም ይሁን በከፊል ከመንግስት በሚመደብለት በጀት የሚተዳደርንና የፋይናንስ እንቅስቃሴው በመንግስት ቁጥጥር የሚደረግበትን ማንኛውንም መ/ቤት ወይም ተቋም ያካትታል።
25) መደበኛ በጀት፡- ቋሚ ንብረቶችን ለመፍጠር የማይውልና መንግስታዊ ስራዎችን ለማከናወን የሚያስፈልጉ ወጪዎችን ለመሸፈን የሚዉል በጀት ሲሆን ይህም ለደመወዝ ክፍያ እና ለዕቃዎችና አገልግሎቶች ግዥ የሚዉሉ ወጪዎችን የሚያካትት ነው፡፡
26) ተንከባላይ ወጪ፡- ከአንዱ በጀት ዓመት ወደ ሚቀጥለው የሚንከባለልና በየጊዜው የሚታደስ ወጪን ያመለክታል፡፡
27) ዘላቂ የልማት ግቦች፡- ለሁሉም የተሻለ እና ቀጣይነት ያለው ምቹ ሁኔታን ለመፍጠርና ዓለም ዓቀፍ ተግዳሮቶች ማለትም ድህነትን፣ ኢ-ፍትሃዊነትን፣ የአየር ንብረት ለውጥንና የአካባቢ ብክለትን ለመቅረፍ እንዲሁም ሰላምን ለማስፈን የተወጠኑ ዓለም አቀፍ ግቦች ናቸው፡፡

ማጣቀሻ/ዋቢ

- የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳዳር አስፈጻሚ አካላት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 84/2016
- የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳዳር የፍኖተ-ብልጽግና ማክሮ ኢኮኖሚና ፊስካል ማዕቀፍ 2013
- የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳዳር የመካከለኛ ዘመን የወጪ ማዕቀፍ ጥናት (2018-2020)
- የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳዳር የ2018 በጀት ዓመት የበጀት አዋጅ/ረቂቅ
- የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳዳር ፋይናንስ ቢሮ የገቢና ወጪ ሪፖርት (2014-2017)
- የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የዜጎች በጀት መረጃ ሰነድ አዘገጃጀት መመሪያ 2014 ዓ.ም
- የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳዳር የበጀት ዝግጅት ማኑዋል 2006 ዓ.ም
- የኢትዮጵያ ህገ-መንግስት አንቀጽ 89 ንዑስ አንቀጽ 6፣ 1987
- የተሻሻለው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ማቋቋሚያ ቻርተር አዋጅ ቁጥር 361/1995
- የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 51/2009
- የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የፋይናንስ ግልጽነትና ተጠያቂነት ስርዓት መተግበሪያ መመሪያ ቁጥር 05/2011

ለበለጠ መረጃ፡

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከተማ የፋይናንስ ቢሮ

አዲስ አበባ/ ኢትዮጵያ

ስልክ፡-መደበኛ፡ +251 ; **ሞባይል**: +251913284645;

aabof.com.et

Addis Ababa City Administration Bureau of Finance

https://www.facebook.com/aabof.gov.et?mibextid=ZbWKwL

https://t.me/AACABOFP

aabof PUBLIC

https://chat.whatsapp.com/FLSn12vRmsR9JsKUVDWxgtuuuu

Addis Ababa City Administration Finance Bureau

youtube.com/channel/UCTPN7Re7T7tp_ekAhVuw2uA

በተጨማሪም ዘወትር ሐሙስ ጠዋቱ 2፡00-2፡20 **በአዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ ኤፍ ኤም** 96.3 **ይከታተሉን።**